Pegasus
partners in health
kia atawhai ki te tangata



# የኒውዚላንድ የጤና አጠባበቅ መዋቅር

Amharic

# የኒውዚላንድ የጤና አጠባበቅ መዋቅር

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር (MOH) 20 የክልል የጤና ቦርዶችን ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል እንዲሁም ይደጉማል። እያንዳንዳቸው የክልል ጤና ቦርዶች ደግሞ በየክልላቸውን የጤና አጠባበቅ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚያወጣው የጥራት ደረጃ መሰረት ያስተናብራሉ።

በኒውዚላንድ ውስጥ ብዙ የህክምና አገልግሎቶች ነፃ ወይም ቅናሽ ናቸው። የዚህን አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን የኒውዚላንድ ዜጋ፣ ቋሚ ነዋሪ፣ ቢያንስ የሁለት ዓመት የስራ ፈቃድ ወይም የስደተኛ ኮታ ፈቃድ ሊኖርዎት ይገባል ። እነዚህን የማያሟሉ ከሆነ ለህክምና አገልግሎቶች ሙሉ ሊከፍሉ ይችላሉ።  የድንገተኛ ህክምናን ግን መክፈል ባይችሉም እንኳ አይከለከሉም። የኒውዚላንድ የጤና አጠባበቅ መዋቅር በሁለት ተከፍሎ የመጀመሪያ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ የጤና አጠባበቅ በመባል ይታወቃል። የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አጠባበቅ ወይም የህክምና አገልግሎት የቤተሰብ ሀኪሞችን፣ ስፔሻሊስቶችን (በሆስፒታሎች ውስጥም ሊሰሩም ይችላሉ)፣ የጥርስ ሀኪሞችን፣ ወጌሻዎችን (ፊዚዮቴራፒ)፣ የእግር ሀኪሞችን (ፖዲያትሪስት) ፣ አማካሪዎችንና የመሳሰሉትን ያካትታል። የሁለተኛ ደረጃ ህክምና ደግሞ በህዝብ ወይም በግል ሆስፒታሎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ያካትታል።

የነፃ ህክምና መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የህክምና አገልግሎቶች በሀገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ የህዝብ የህክምና መስጫ ተቋማት ሊያገኙ ይችላሉ።

- በህዝብ ሆስፒታሎች ውስጥ የነፃ ህክምና
- በማንኛውም የህዝብ ሆስፒታል የ24 ሰዓት ነፃ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት
- የማዘዣ መድሃኒቶችን በቅናሽ ዋጋ ማግኘት
- የቤተሰብ ሀኪምዎ ጋር በቅናሽ ዋጋ መታከም፤ በሀኪሙ የተመዘገቡ ከሆነ ደግሞ ጥሩ ቅናሽ ሊያገኙ ይትላሉ
- የቤተሰብ ሀኪምዎ ወደ ከፍተኛ የአዕምሮ ሀኪም፣ ወጌሻ፣ ወይም የአጥንትና የጡንቻ ሀኪም ሪፈር በሚጽፍበት ጊዜ አገልግሎቱን በቅናሽ ዋጋ ማግኘት
- ፅኑና ከባድ ህመም ካልብዎት የነፃ ወይም የቅናሽ ህክምና ማግኘት
- አብዛኛዎችን የላብራቶሪና የራጅ ምርመራዎች በነፃ ማግኘት (ምርመራው የሚካሄደው በግል የህክምና መስጫ ማዕከል ከሆነ ግን ሙሉ ክፍያውን ሊከፍሉ ይችላሉ። በተጨማሪም ለስራ ቅጥር ወይም ለስልጠና የሚያስፈልጉ የላብራቶሪም ሆነ የራጅ ምርመራዎችን ወጭ አያካትትም)
- ከግል ሀኪም ቤቶች በስተቀር በእርግዝናና በወሊድ ሰዓት ነፃ ህክምና ማግኘት። ነገርግን ህክምናውን በግል ሀኪም ቤቶች በነፃ ሊያገኙ አይችሉም
- የቤተሰብ ሀኪምዎን ለማማከር በመጀመሪያ ቀን ከሚከፍሉት ክፍያ ውጭ ነፃ የሪፈራል አገልግሎት ማግኘት
- እድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት የነፃ ወይም የቅናሽ ህክምና ወይም  የማዘዣ መድሃኒት ማግኘት። ብዙ ጊዜ ለትናንሽ ህፃናት የዶክተሮች እንዲሁም የማዘዣ መድሃኒት ዋጋ ነፃ ነው።
- እድሜያቸው ከ45 እስከ 69 ለሆኑ ሴቶች ነፃ የጡት ካንሰር ምርመራ ማግኘት
- አስፈላጊ ከሆነ ነፃ የማህፀን ካንሰር ምርመራ ማግኘት

የነፃ ህክምና መስፈርቶችን በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ድህረ ገፅ ላይ ሊያገኙ ይችላሉ። ለመመሪያዎቹ  ይህንን ድህረ ገፅ ይጫኑ

 Guide to eligibility  for publicly funded health services (በህዝብ የሚደጎሙ የነፃ ህክምና መስፈርቶች መመሪያ)። ይህም ድህረ ገፅ በዋናው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ድህረ ገፅ http://www.health.govt.nz/  ውስጥ ይገኛል።

ለብዙ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና ክፍያ ሊከፍሉ ይችላሉ። ነገር ግን የተመዘገቡ ታካሚ ከሆኑና የቤተሰብ ሀኪምዎን ወይም ነርስ በሚያማክሩበት ጊዜ ቅናሽ ሊያገኙ ይችላሉ። በመሆኑም የጠቅላላ ክፍያውን 50% ሊከፍሉ ይችላሉ። የተመዘገቡና እድሜያቸው ከ 6 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት ህክምናና የማዘዣ መድሃኒት በነፃ ያገኛሉ።

መስፈርቱን ለሚያሟሉ ግለሰቦች በኒውዚላንድ ሆስፒታሎች ህክምና ነፃ ነው። የሆስፒታል ህክምና ለማግኘት ግን በስፔሻሊስት ሀኪም ሪፈር ሊፃፍልዎት ይገባል። ያሉበት ሁኔታ አስቸኳ ወይም አፋጣኝ ከሆነ የቤተሰብ ሃኪምዎ ሪፈሩን ሊፅፍልዎት ይችላል። ነገርግን በፅኑ ህመም ወይም በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ወደ  ሆስፒታል ያልገቡ ከሆነና ከፈለጉ ህክምናዎን በሚፈልጉት የግል ሆስፒታል ሊያከናውኑ ይችላሉ። ሆኖም ግን ሙሉ ወጭውን ይሸፍናሉ። የግል ሆስፒታሎችን ህክምና ለማግኘት የህክምና መድህን ወይም ኢንሹራንስ መግዛት ጠቀሜታ አለው።

የነፃ ህክምናንና የአካል ጉዳተኞች ነፃ ህክምናን መስፈርቶች የማያሟሉ አንዳንድ እናቶች ባለቤቶቻቸው መስፈርቱን የሚያሟሉ ከሆነ በቅናሽ የእናቶች ህክምና አገልግሎት ሊያገኙ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ድህረ ገፅ ይመልከቱ።

Guide to eligibility for publicly funded health services (በህዝብ የሚደጎሙ የነፃ ህክምና መስፈርቶች መመሪያ)። ይህም ድህረ ገፅ በዋናው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ድህረ ገፅ http://www.health.govt.nz/ ውስጥ ይግኛል።

ሁሉም እድሜያቸው ከ 6 ያልበለጡ ህፃናት ምንም አይነት የኢምግሬሽን ሁኔታ ወይም ዜግነት ቢኖራቸውም ክትባት በሚሰጥበት ጊዜ ወይም በ “WellChild” አገልግሎት የነፃ ክትባት ማግኘት ይችላሉ።

የኒውዚላንድ መንግስት ማንኛውም በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙና የነፃ ህክምና መስፈርቶችን የማያሟሉ ግለሰቦችን የህክምናና የጉዞ መድህን እንዲኖራቸው በጥብቅ ያሳስባል።

## የቤተሰብ ሃኪምዎን (GP) ለመምረጥ

የቤተሰብ ሃኪም ወይም ጠቅላላ ሃኪም (GP) የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና ዋና አካል ወይም ቡድን ሲሆን በኒውዚላንድ የጤና ጥበቃ አወቃቀር የታካሚዎች የመጀመሪያ መዳረሻ ናቸው። የቡድኑ አባላት የቤተሰብ ዶክተሩን፣ ነርስ እና የፋርማሲ ወይም የመድሃኒት ባለሞያውን ያካትታል። ወደ አዲሱ የመኖሪያ ቤትዎ ወይም አካባቢ ወይም ከተማ ከመጡ በኋላ የቤተሰብ ሃኪም ጋር በመሄድ መመዝገብ በጣም ጠቃሚ ነው። ብዙዎቹ ጠቅላላ ሃኪሞች በህክምና መስጫ ማዕከሎች ይገኛሉ። ለመመዝገብ የህክምና ምክርቤትን ድህረ ግፅ መመልከት፣ ወይም የ በነጩ የስልክ መፅሃፍ (ዋይት ፔጅስ) (White Pages) ውስጥ “Registered Medical Practitioners and Medical Centres” በሚለው ስር የተመዘገቡ የህክምና ማዕከሎችን ሊያገኙ ይችላሉ፣ ወይም ደግሞ በዌብሄልዝ (WebHealth) ድህረ ገፅ http://www.webhealth.co.nz/home/ የሚፈልጉትን የህክምና አገልግሎት መርጠው በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የህክምና ማዕከል መምረጥ ይችላሉ።

የህክምና መስጫ ማዕከሎች ዶክተሮች፣ነርሶችና የአስተዳደር ሰራተኞች ይኖሯቸዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ የፋርማሲ ባለሞያ፣ ልዩ ልዩ ባለሞያዎችና የማህንበረሰብ አገልግሎት ሰራተኞች ይኖሯቸዋል። ሁሉም ለእርስዎ ጥሩ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ጠቃሚ ሚና አላቸው።

## በዶክተር በምመዘገብበት ጊዜ ምን ይሆናል?

በጠቅላላ ሃኪም ወይም በቤተሰብ ሃኪም ያልተመዘገቡ ከሆነ ለመታከም በሚሄዱበት ጊዜ ብዙ ሊከፍሉ ይችላሉ። ለመመዝገብ የምዝገባ መስፈርቶችን ሊያሟሉ ይገባል። ለመታከም የሚመርጡት ወንድ ወይም ሴት ሃኪም ጋር መመዝገብ ይችላሉ። የሃኪሙ እንግዳ ተቀባይ የመመዝገቢያ ቅፅ እንዲሞሉ ይሰጥዎታል። በሚሞሉበት ጊዜ ሙሉ ስምዎንና አድራሻዎን በትክክል መሙላትዎንና እንዲሁም ፓስፖርትዎንና ቪዛዎን ይዘው መምጣትዎን አይዘንጉ። ሆኖም በፈለጉት ሰዓትና ጊዜ ሃኪም የመቀየር ሙሉ መብት አለዎት። ነገርግን በሚታከሙበት ጊዜ የሚያገኙትን ቅናሽ እስከ 3 ወር ድረስ ላያገኙ ይችላሉ። ስለዚህ በነዚህ 3 ወራት ውስጥ ቅናሽ የሌለው ሙሉ ክፍያ መክፈል ይጠበቅብዎታል። ለተመዘግቡ ታካሚዎች ብዙ አይነት የቅናሽ አገልግሎቶች ይሰጣሉ። በመረጡት የህክምና መስጫ ማዕከል የመመዝገቢያ ቅፁን ሞልተው ካስገቡና ከተመዘገቡ በኋላ የነዚህን የቅናሽ አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

በተጫማሪም በህክምና መስጫ ማዕከል መመዝገብ ከህክምና ቡድንዎ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖርዎ ይረዳዎታል።

## የቤተሰብ ሃኪሜ ጋር ቀጠሮ የምይዘው እንዴት ነው?

ቤተሰብ ሃኪምዎ ጋር መሄድ ሲፈልጉ አንድ ቀን ቀደም አድርገው በመደወል ቀጠሮ ማስያዝ ይኖርብዎታል። ያሉበት ሁኔታ አስቸኳይ ከሆነ ግን ሃኪምዎ በተመሳሳይ ቀን ያክምዎታል። ወደ ጤና ማዕከሉ ሲመጡ ከፈለጉ ረዳት የሚሆንዎን ሰው ይዘው መምጣት ይችላሉ። ነገርግን ያመጡት ሰው እንደ አስተርጓሚ ሊያገለግልዎ አይችልም። ምክንያቱም ይህ አገልግሎት በሰለጠኑ አስተርጓሚዎች ብቻ የሚሰጥ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ቆየት ብለን እንወያያለን።

ነርሶች ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ አጠቃላይ ጤናን በተመለከተ ለሚፈልጉት መረጃ ዋነኛ ምንጮች ናቸው። ነርስ ለማነጋገርም ቀጠሮ አስፈላጊ ስለሆነ መጠየቅ ይቻላል።

ሁልጊዜ በሃኪም በሚታዩበት ጊዜ የአገልግሎት ክፍያ አስፈላጊ ነው። የክፍያው መጠን እንደየጤና ማዕከሉ ሊለያይ ይችላል። ሃኪምዎ እቤትዎ ድረስ መጥቶ የሚያክምዎ ከሆነ ወይም የድንገተኛ ህክምና በሚያደርጉበት ጊዜ ተጨማሪ ክፍያዎች ሊኖሩ ይችላሉ።

በሚታከሙበት ጊዜ ዶክተሩ እንዳስፈላጊነቱ የመድሃኒት ማዘዣ ሊሰጥዎት ይችላል። ሁሉም ህመም በኢንፌክሽን ምክንያት አይመጣም። አንዳንድ የመተንፈሻ አካል ኢንፌክሽኖች በቫይረስ የሚመጡ ሲሆኑ በፀረ ባክቴሪያ (አንቲ ባዮቲክስ) መድሃኒት ሊድኑ አይችሉም። ሃኪምዎ ፀረ ባክቴሪያ መድሃኒት ካዘዘልዎ ሁሉንም በታዘዙት መሰረት መወሰድ ይኖርብዎታል። ፀረ ባክቴሪያ(አንቲ ባዮቲክስ) እና ፀረ እብጠት (አንቲ ኢንፍላሜቶሪ) መድሃኒቶች አገልግሎታቸው እንደሚለያይ አይዘንጉ።

## ስፔሻሊስት ሃኪም ጋር ለመሄድ

የቤተሰብ ሃኪምዎ ወደ ስፔሻሊስት ሃኪም እንዲሄዱ ሪፈር ሊፅፍልዎ ይችላል። የስፔሻሊስት ሃኪም ክፍያ እንደየሃኪሙ ቢለያይም ለመጀመሪያ ጉብኝት ከ 150.00 ዶላር ይጀምራል። ክፍያውን እራስዎ ወይም የጤና መድህንዎ ከከፈለ ህክምናውን ባፋጣኝ ሊያገኙ ይችላሉ።

በህዝብ የሚደጎምን የህክምና አገልግሎት መስፈርቶች ካሟሉ  የቤተሰብ ሃኪምዎ  በህዝብ የጤና ማዕከል ወደሚገኝ ስፔሻሊስት ሃኪም ሊመራዎት ይችላል። ህክምናው ሙሉ በሙሉ ነፃ ቢሆንም የታካሚዎች ወረፋ ካለ ብዙ ወራትን ሊጠብቁ ይችላሉ።

## የግል የጤና መድህን የሚሰራው እንዴት ነው

አንዳንድ ኒውዚላንዳዊያን የግላቸውን የጤና መድህን (ኢንሹራንስ) መግዛትን ይመርጣሉ። የጤና መድህን መግዛት ወድ ቢሆንም መድህን አለዎት ማለት የስፔሻሊስት ሃኪምንና  የግል ሆስፒታል ህክምናን ምንም ወረፋ ሳይጠብቁ ማግኘት ይችላሉ። ብዙውን ጊዜም የህክምና ወጭዎን መድህንዎ ይሸፍናል። ስለ ጤና መድህን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በ የሎው ፔጅስ "yellow pages" ድህረ ገፅ http://www.yellow.co.nz  "Insurance – Medical in Christchurch"  በሚለው ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ።

አንዳንድ የመድህን ሰጭ ድርጅቶች ሌላ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ባለሞያዎች አሏቸው። ብዙውን ጊዜ በጎሳ (ኢትኒክ) መልዕክት ማሰራጫ ዘዴዎች ያስተዋውቃሉ።

ስለ ጤና መድህን በ "Everybody" ድህረ ገፅ ላይ ተጨማሪ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ። ድህረ ገፁ http://www.everybody.co.nz/page-56d7ef0e-9e87-46ad-9ab9-843e76f8301e.aspx ነው።

# የኮሚኒቲ ሰርቪስ ካርድ

የኮሚኒቲ ሰርቪስ ካርድ በ(ወርክ ኤንድ ኢንካም) (ዊንዝ) የተባለ የመንግስት አካል የሚሰጥ ካድር ነው። ከሚከተሉት አንዱን መስፈርት የሚያሟሉ ከሆነ የኮሚኒቲ ሰርቪስ ካርድ ማግኘት ይችላሉ።

- እድሜ ከ 18 አና ከዛ በላይ ከሆነ ወይም ከ16-17 ዓመት ከሆነና በቀን ፕሮግራም የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ ከሆኑ
- ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ገቢ ያለው (መጠኑ በቤተሰብ ሁኔታ ይወሰናል)
- የኒውዚላንድ ዜጋ ወይም ቋሚ ነዋሪ ከሆኑ

ካርዱ የሚከተሉትን አገልግሎቶች በቅናሽ ዋጋ ወይም ያለምንም ክፍያ እንዲያገኙ ያስችልዎታል።

- ከስራ ሰዓት ውጭ ለሚደረጉ የህክምና ወጭወች
- የቤተሰብ ሃኪምዎን ሳይሆን ሌላ ሃኪም በሚጎበኙበት ጊዜ
- እድሜያቸው 15 እና ከዚያ በታች ለሆኑ ህፃናት በሃኪም የታዘዘ መነፀር መግዣ
- በሆስፒታሎች ወይም ፈቃድ ባላቸው የጥርስ ህክምና ማዕከሎች የድንገተኛ ጥርስ ህክምና ለማድረግ
- ከአካባቢዎ ራቅ ወዳለ ሆስፒታል ሄደው የሚታከሙ ከሆነና የቤት እርዳታ እንደሚያስፈልግዎ ከታወቀ የመጓጓዣና የማረፊያ ወጭን
- የማዘዣ መድሃኒት መግዣ (ለምሳሌ ከግል የጤና ህክምና መስጫ ስፔሻሊስት የታዘዙ)። በህዝብ ሆስፒታሎችና በመሰረታዊ የጤና ድርጅት የተፃፉትን አያካትትም።

ስለ ካርዱ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሚከተለውን ድህረ ገፅ ይመልከቱ http://www.workandincome.govt.nz/individuals/a-z-benefits/community-services-card.html

የኮሚኒቲ ካርድ ለማውጣት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች በበለጠ ለማወቅ ዊንዝን በማነጋገር፣ የተመደቡ የመንግስት ተወካዮችን በማነጋገር፣ የሚከተለውን ድህረ ገፅ በመመልከት ወይም በ 0800 999 999 የነፃ ስልክ በመደወል ማግኘት ይችላሉ። http://www.workandincome.govt.nz/

## የብዙ ህክምና ተጠቅሚ (High Health user) ካርድ ምንድን ነው

የቤተሰብ ሃኪሞቻቸውን ለህክምና በዓመት 12 ጊዜና ከዚያ በላይ የሚጎበኙ ታካሚዎች የብዙ ህክምና ተጠቃሚ ካርድን ማግኘት ይችላሉ። ይህ ማለት ለህክምናዎ ወይም ለመድሃኒት ወጭዎ ጥሩ ቅናሽ እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

## አደጋ ቢያጋጥመኝ

የኒውዚላንድ ዜግነት፣ቋሚ ነዋሪነት፣ጊዚያዊ ቪዛ ያለዎትና በስራ ቦታ ወይም በቤት ስራ በአደጋ ምክንያት ቢጎዱ የመንግስት የአደጋ መድህን ድርጅት ኤሲሲ (ACC) የሚፈለገዉን ክፍያ ሊሸፍን ይችላል። ነገርግን ኤሲሲ (ACC) ነፃ ህክምና እንዲያገኙ የማድረቅ አቅም የለውም። ስለዚህ የህክምና ወጭውን ሊከፍሉ ይችላሉ። የ ኤሲሲ (ACC) ተጠቃሚ ለመሆን አንዳንድ መስፈርቶችን ማሟላት ያስፈልጋል። መንስኤው አደጋ ያልሆነ ህመም፣ ጭንቀት፣ የመንፈስ መረበሽ፣ የእርጅና ህመምና ቀስ በቀስ የሚመጣ ጉዳትን የኤሲሲ መድህን አያካትትም። ለተጨማሪ መረጃ በነፃ ስልክ ቁጥር 800 101 996 በመደወል ወይም በኤሲሲ ድህረ ገፅ ማግኘት ይችላሉ። ድህረገፁም http://www.acc.co.nz/

**ያስታውሱ** የኤሲሲ መድህን በየትኛውም የኢምግሬሽን ሁኔታ ውስጥ ቢገኙም በሀገሪቱ ውስጥ ለደረሱ የአደጋ ጉዳቶች ሽፋን ይሰጣል።

አስተርጓሚዎችንም በቋንቋ መስመር (Language Line) ውስጥ ማግኘት ይችላሉ።

## ከስራ ሰዓት ውጭ የሚደረግ ህክምና

በቤተሰብ ሃኪምዎ የስራ ሰዓት (ከ 8am-6pm) ውጭ የአስቸኳይ ህክምና ከፈለጉ ወደ የህክምና መስጫ ጣቢያው በመደወል ዶክተርዎን ማነጋገር ይችላሉ። ሃኪምዎ የስልክ ጥሪውን ማንሳት ካልቻለ ግን ጥሪው ወደ ነርስ ስለሚዞዋወር አስፈላጊውን እርዳታና ምን ማድረግ እንዳለብዎት መወያየት ይችላሉ።

ሄልዝ ላይን (Health line) የ 24 ሰዓት ነፃ የስልክ አገልግሎት መስጫ ነው። ከተመዘገበ ነርስ ነፃ ምክር ለማግኘት በነፃ ስልክ ቁጥር 0800 611 116 ይደውሉ። አገልግሎቶችን በራስዎ ቋንቋ ማግኘት ከፈለጉም አስተርጓሚ መጠየቅ ይችላሉ።

በአካል ተገኝተው ሃኪም ማነጋገር ከፈለጉም የ24 ሰዓት አገልግሎት ወደሚሰጡ የህክምና ማዕከሎች በመሄድ ማነጋገር ይችላሉ። ለአገልግሎቱ ክፍያ ሊያስፈልግ ይችላል። የሚጠብቁት ወረፋም ከሆስፒታሎች አንፃር አነስተኛ ነው።

የ24 ሰዓት የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት በመንግስት ሆስፒታሎች የድንገተኛ ህክምና ክፍል ውስጥ ይሰጣል። ለዚህ አገልግሎት ምንም ክፍያ ወይም ቀጠሮ አያስፈልገውም። አንዳንድ ጊዜ ግን ለመታከም ወረፋ ሊጠብቁ ይችላሉ። ድንገተኛ ኣደጋ ወይም ፅኑ ህመም ካጋጠምዎት ወደ ድንገተኛ ህክምና ክፍል መሄድ ይኖርብዎታል።

## የአምቡላንስ አገልግሎት

ለብዙ ኒውዚላንዳዊያን ሴንት-ጆን (St. John) የአምቡላንስ አገልግሎትን ይሰጣል። በአደጋ ጊዜ ወደ አምቡላንስ ለመደወል የስልክ ቁጥር 111ን ይጠቀሙ።

የየአምቡላንስ አገልግሎት ነፃ እንደሆነ ቢታወቅም ድንገተኛ ላልሆነ አገልግሎት ከተጠቀሙ የክፍያ ወረቀት በአድራሻዎ ሊላክልዎት ይችላል። ሴንት-ጆን የእርዳታ ሰጭ ድርጅት በመሆኑና ክፍያቸው 80 ዶላር ብቻ ስለሆነ ቢከፍሉም እንደ እርዳታ ይቆጠራል።

የ አምቡላንስ ሰራተኞች የሰለጠኑና አደጋ የደረሰባቸውን ወይም በፀና የታመሙ ግለሰቦችን ተገቢውን ህክምና እስከሚያገኙ ድረስ በመንከባከብ በተሻለ ሁኔታ ውስጥ እንዲቆዩ ይረዳሉ። አገልግሎታቸው በዝርዝር

- የታመሙ ሰዎችን ወደ ሆስፒታል ማጓጓዝ
- ታማሚዎችን ከሆስፒታል ወደ ሌላ ሆስፒታል ወይም ከሆስፒታል ወደ ቤት ማጓጓዝ
- ከእሳት አደጋና ከፖሊስ ጋር በመተባበር በአደጋ ጊዜ የህክምና አገልግሎት መስጠት
- የአውሮፕላን አምቡላንስ አገልግሎቶችን ማመቻቸት
- የግለሰቦችን የህክምና ደዎልን ወይም ሜዲካል አላርም (Medical Alarm) ማስተናበር

## የጥርስ ህክምና እንዴት ማግኘት እችላለሁ

መሰረታዊ የጥርስ ክህምና ከውልደት እስከ 18ኛ የልደት ቀን ድረስ ለህፃናት በነፃ ይሰጣል። ከዚያ በኋላ ግን ለጥርስ ህክምና ይከፍላሉ። ብዙ ግለሰቦች በግል የጥርስ ሃኪም ለመታከም ይመዘገባሉ ክፍያውንም ይከፍላሉ።

የጥርስ ሃኪሞችም እንደ የቤተሰብ ሃኪሞች ለህክምናዎ አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶችን ሊያዙ ይችላሉ። የታዘዘልዎትን መዲሃኒቶች በአቅራቢያዎ በሚገኝ ፋርማሲ መወሰድ ይችላሉ።

ብዙውን ጊዜ የጥርስ ሃኪሞች በመንግስት ድጎማ ስለማይደረግላቸው ክፍያቸው ከሌሎች በላይ ነው።

በየሎው ፔጅስ (yellow pages) ድህረ ገፅ ወይም በኒውዚላንድ የጥርስ ህክምና ካውንስል (Dental council of New Zealand) ድህረ ገፅ ውስጥ የጥርስ ሃኪሞችን ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ። በአካባቢዎ የሚገኝን የጥርስ ሃኪም ለማግኘት የሚከተለውን ድህረ ገፅ ይመልከቱ። http://www.dentalcouncil.org.nz/

## የፋርማሲ ወይም የመድሃኒት ቤት አገልግሎት እንዴት ማግኘት እችላለሁ።

ያሉበት የጤና ሁኔታ መድሃኒት ካስፈለገው ሃኪምዎ መድሃኒት ያዝዝልዎታል። (በኒውዚላንድ የማዝዣ መዲሃኒቶች በየትኛውም መዲሃኒት ቤት ያለ ሃኪም ማዘዣ አይሰጡም። ስለዚህ የማዘዣ ወረቀቱን ወደ መዲሃኒት ቤቱ መውሰድ ኣለብዎት። የማዘዣ ወረቀቱን ለባለሞያው ከሰጡ በኋላ መዲሃኒቱ እስከሚሰጥዎ ድረስ ምን ያክል ጊዜ እንደሚፈጅ ይነገርዎታል። (የፋርማሲ ባለሞያው ስራ በሚበዛበት ጊዜ እስከ 20 ደቂቃ ሊወስድ ይችላል።) መድሃኒቱን ከመረከብዎ በፊት የመዲሃኒት መደብር ባለሞያው ስምዎንና አድራሻዎን እንዲያረጋግጡ ይጠይቅዎታል። ይህ የሚደረገው በትክክል የታዘዘልዎትን መዲሃኒት መቀበልዎን ለማረጋገጥ ነው። የቤተሰብ አባላትዎም መድሃኒቱን ተቀብለው መውሰድ ይችላሉ።

የተፈቀደላቸው ግለሰቦች ለሚወስዱት እያንዳንዱ መድሃኒት 5 ዶላር ይከፍላሉ። የብዙ መድሃኒቶች ዋጋ በመንግስት የተሸፈነ ነው። ነገርግን አንዳንድ መድሃኒቶች ዋጋቸው ብዙ ከመሆኑ የተነሳ አይሸፈኑም። በዚህ ጊዜ ከ 5 ዶላሩ በተጨማሪ ሊከፍሉ ይችላሉ። በተደጋጋሚ ከፋርማሲው የሚወሰዱ መድሃኒቶች ካልዎት ግን ሁልጊዜ በመጡ ቁጥር 5 ዶላሩን አይከፍሉም። መድሃኒቱን ቀኑ ከመቃጠሉ በፊት(ብዙውን ጊዜ 3 ወር ነው) ከተመሳሳይ ፋርማሲ መውሰድ ይኖርብዎታል። መድሃኒትዎን ተመላልሰው መውሰድ የማይችሉ ከሆነ ሁሉንም አንድ ጊዜ ለመውሰድ መጠየቅ ይችላሉ።

መድሃኒቱን በሚቀበሉበት ጊዜ እባክዎን እንዴት መወሰድ (መዋጥ) እንዳለበት መረዳትዎን አይዘንጉ። ከተጠራጠሩ ግን የፋርማሲ ሰራተኞችን ይጠይቁ። ሌላ ተጨማሪ የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ደግሞ የፋርማሲ ባለሞያውች ቡድን እቤትዎ ድረስ በመምጣት ምክር ሊሰጥዎት ይችላሉ። ይህ ተንቀሳቃሽ የመድሃኒት አወሳሰድ አገልግሎት ስለ መድሃኒት አወሳሰድ ምክርና ትምህርት የሚሰጡ የፋርማሲ ባለሞያወች ስብስብ ነው። አስተርጓሚዎችም ኣብረው ሊኖሩ ይችላሉ።

ተጨማሪ መረጃ ከፈልጉ የሚከተሉትን ድህረ ገፆች ይመልከቱ

http://www.pharmac.health.nz/

http://www.pharmac.govt.nz/patients

ቤተሰብዎ ወይም እርስዎ ለመድሃኒት የሚከፍሉት ብዙ ከሆነ የመድሃኒት ክፍያ ማስቀነሻ ካርድ (Pharmaceutical Subsidy Card) በአቅራቢያዎ በሚገኝ ፋርማሲ ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ።

ፋርማሲዎች ከማዘዣ መድሃኒቶች በተጨማሪ የተለያዩ ከጤና ጋር ግንኙነት ያላቸው እቃውችንም ይሸጣሉ። እነሱም ለተለያየ የጤና ችገር ሊዉሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ለትኩሳት፣ ለማስታገሻና ለመሳሰሉት። ምክር ለማግኘትም የፋርማሲ ሰራትኛ ይጠይቁ።

የፋርማሲ ባለሞያዎች እንዲሁም ሰራተኞች ስለ ራስዎ ወይም ቤተሰብዎ ጤና ጥያቄ ካልዎት ምክር ሊሰጥዎ ይችላሉ።

ፋርማሲዎች ከሚከፈቱበት ሰዓት ውጭ አስቸኳይ መድሃኒት ከፈለጉ ወደ አስቸኳይ ፋርማሲዎች ይሂዱ። እነዚህ ፋርማሲዎች እስከ 10pm ወይም 11 pm ሰዓት ድረስ ክፍት ይሆናሉ። በ ኋይት ፔጅስ (white pages) መፅሃፍ "Hospitals & other health service providers" በሚለው ስር "Urgent Pharmacies" ውስጥ አስቸኳይ ፋርማሲዎች ማግኘት ይችላሉ።

## አስተርጓሚዎችን እንዴት ማግኘት እችላለሁ

ከሃኪምዎ ጋር በራስዎ ቋንቋ በደንብ ለመግባባትና ሃኪምዎን በደንብ ለመረዳት አስተርጓሚ የማግኘት መብት አለዎት። ይህ አገልግሎት ለተመዘገቡ ታካሚዎች ነፃ ነው። ከ24 ሰዓት በፊት ቀጠሮ በሚያስይዙበት ጊዜ አስተርጓሚ እንደሚፈልጉ ይጠይቁ። ልጆችን ወይም የቤተሰብ አባላትን እንደ ኣስተርጓሚ አይጠቀሙ። የጤና ባለሞያዎች ስላልሆኑ የሃኪሙን ምክርና መመሪያ በቀላሉ ሊያሳስቱት ይችላሉ።

## ስለ ጤና አገልግሎቴ ቅሬታ እንዴት ማቅረብ እችላለሁ

ማንኛውም የህክምና ወይም የአካል ጉዳተኞችን አገልግሎት የሚጠቀም ግለሰብ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ገለልተኛ የሆነ የመንግስት ኮሚሽነር በኒዚላንድ ህግ መሰረት ይህንን ተግባራዊ ያደርጋል። እነዚህ መብቶች በራስዎ ቋንቋ በሚከተለው ድህረ ገፅ ላይ ይገኛሉ።

http://www.hdc.org.nz/

## ነፃ የስነ፡ጤና ምክርና ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

በቤተሰብ ሃኪምዎ፣ በጥርስ ሃኪምዎ ወይም በስፔሻሊስት ሃኪምዎ ከታከሙ በኋላ የጤና ሁኔታዎን ስምና የድህረ ገፅ ኣድራሻ የያዘ ካርድ ሊሰጥዎት ይችላል። ድህረ ገፁን ከከፈቱ በኋላ የጤና ሁኔታዎን ስም ሲያስገቡ ስለጤናዎ ሁኔታ በደንብ ወደሚገልፅ ሌላ ገፅ ይመራዎታል። ሌሎች ተጨማሪ ገፆችም በራስዎ ቋንቋ በመተርጎም ላይ ናቸው።

http://www.healthinfo.org.nz/

ስለ አካባቢዎ የስነ፡ጤና አገልግሎት ነፃ ምክር ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ በ "health line" የነፃ ስልክ ቁጥር 0800 611 116 ይደውሉ።

ስለ ኒውዚላንድ ኑሮ አጠቃላይ መረጃዎች ወይም የስነ፡ጤና መረጃዎችን ከፈለጉ በ ክራይስትቸርች (166 ሴንት አስፋህ መንገድ) በሚገኘው የክራይስትቸርች መጤዎች ማዕከል "Christchurch Migrants Centre" ድርህረ ገፅ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

http://www.migranthub.org.nz/

በተጨማሪም ስነ፡ጤናን በተመለከተ በሌሎች ቋንቋዎች መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ድህረ ገፅ ይመልከቱ

https://www.healthed.govt.nz/

Pegasus
partners in health
kia atawhai ki te tangata

©Pegasus Health (Charitable) Ltd, PO Box 741, Christchurch - AM001

Printed 1st May 2014